የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)

**አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ**

# ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለሰላምና መረጋጋት ከኢሰመጉ የቀረበ ጥሪ

የካቲት 03/2015 ዓ.ም

## መግቢያ፡

ኢሰመጉ በተለያዩ ጊዜዎች በሀገሪቱ የሚነሱ የተለያዩ ውጥረቶችን ተከትሎ ለሀገር ሰላምና መረጋጋት የበኩሉን ዘርፈ ብዙ አስተዋጾ ሲያደርግ የቆየ ከማናቸውም አድልዎ ነፃና ገለልተኛ የሆነ መንግስታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ጋር ተያይዘው የሚነሱ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮችን ሲከታተል ቆይቶ ጥር 30 ቀን 2015 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ የደረሱ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በማመላከት መንግስት አፋጣኝ የሆነ ተገቢ መፍትሔ እንዲያበጅ ጥሪ ማቅረቡ ይታወሳል፡፡ ይሁንና ለጉዳዩ ተገቢ የሆነ በቂ ትኩረት እና ማስተካከያ ባለመደረጉ ጉዳዩ አሳሳቢነቱን በመቀጠል በአንዳንድ አካባቢዎች ግድያ፣ እስራት፣ ድብደባና ማዋከብ እየተፈጸመ ይገኛል። ለእዚህም ማሳያነት በወለቴ አካባቢ እና በአየርጤና አካባቢ በትላንትናው እለት ማለትም የካቲት 02 ቀን 2015 ዓ.ም የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በእምነቱ ተከታዮች ላይ ተፈጽመዋል እንዲሁም ከአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ የተለያዩ ዜጎች በትራንስፖርት ወደ አዲሰ አበባ እንዳይገቡ ከመንገድ እየተመለሱ መሆኑን እና በእዚህም ምክንያት በርካታ ቁጥር ያላቸው መንገደኞች እየተንገላቱ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

የፀጥታ ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል ወቅታዊ የጸጥታ ጉዳይን አስመልክቶ የካቲት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ ግብረ-ኃይሉ ለቤተክርሰቲያኗ አባቶች እና ለዕምነቱ ተከታዮች የሚደረገውን የደኅንነት ጥበቃ ለማጠናከር በሚያስችል መልኩ እንደሚቀጥል ገልፆ የነበረ ቢሆንም በአንዳንድ አካባቢዎች በመንግስት የጸጥታ አካላት ከህግ ውጪ ግድያዎች፣ እስራት፣ ድብደባ እና ማዋከቦች ተፈጽመዋል፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ መረጃዎችን የሚያጋሩ የነበሩ ሰዎችን ከመኖሪያ ቤታቸው የመንግስት የጸጥታ ህሎች ነን በሚሉ ሰዎች መወሰዳቸውን እና ያሉበትም እንደማይታወቅ ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

በመጨረሻም የፀጥታ ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል ወቅታዊ የጸጥታ ጉዳይን አስመልክቶ የካቲት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ የካቲት 5 ቀን 2015 ዓ.ም በሚመለከተው አካል የተፈቀደ ሰልፍ እንደሌለ ያሳወቀ ሲሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የካቲት 2 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠው መግለጫ መንግስት የማስተካከያ እርምጃን የማይወስድ ከሆነ የካቲት 5 ቀን 2015 ዓ.ም ሰላማዊ ሰልፍ የምታከናውን መሆኑንና የመንግስት ድርሻ ሰልፉ ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ መንግስታዊ ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት እንደሆነ የገለጸች ሲሆን፤ ቤተክርስቲያኒቱም ትሁን፣ መንግስት፣ የፀጥታ ሀይሎች እንዲሁም ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ከሰላማዊ ሰልፉ ጋር ተያይዞ ምንም አይነት ጥፋቶች እንዳይከሰቱ ከፍተኛ ጥንቃቄን እንዲያደርጉ ኢሰመጉ ጥሪውን አበክሮ በድጋሚ ያቀርባል፡፡

## ተያያዥ የህግ ድንጋጌዎች፡

የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 27 የሀይማኖት ነጻነት መብትን የያዘ ሲሆን በአንቀጽ 11(3) ላይ መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ እና ሀይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንደማይገባ ይደነግጋል፡፡ የእዚህ ንዑስ አንቀጽ ዋነኛ አላማ ከህገ መንግስቱ ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው ሀይማኖትን ከመንግስት ጣልቃ ገብነት እና ከፖለቲካ ጫና ነጻ እንዲሆን በማድረግ የዜጎችን የእምነት ነጻነት ላለመገደብ ሲሆን መንግስት በሀይማኖት ተቋማት መንፈሳዊ ስራ ላይ ጣልቃ መግባት እንደሌለበት ይገልጻል፡፡

በተጨማሪም መንግስት የማህበረሰቡን ደህንነት እና ሰላማዊ መስተጋብር የማስከበር እንዲሁም የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበት ከህገ-መንግስቱ አንቀጽ 13 እና ከህገ መንግስቱ ማብራሪያ አገላለጽ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም መብት በአፍሪካ ቻርተር የግለሰቦች እና ህዝቦች መብቶች አንቀጽ 8 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ እና የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን አንቀጽ 18 ላይ ማንኛውም ሰው የሀሳብ፣ የህሊናና የሀይማኖት ነጻነት እንዳለው ይደነግጋሉ፡፡

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- የፌደራል መንግስት እንዲሁም ችግሮች እየተፈጠረባቸው የሚገኙ የሚመለከታቸው የክልል መንግስታት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀያማኖት ተከታዮች ላይ የሚፈጽሙትን ከህግ አግባብ ውጪ የሆነ ግድያ፣ አካል ማቁሰል፣ ድብደባ እና እስር በአስቸኳይ እንዲያቆሙ፣
- ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ በተገቢው የህግ ስነስርዓት ውጪ እስራት የተፈጸመባው ሰዎችና በመንግስት የጸጥታ አካላት ተይዘው ያሉበት የማይታወቁ ሰዎችን መንግስት እንዲፈታ፣
- ነገሮች ተባብሰው ወደማይመለስ ጥፋት ከማምራታቸው በፊት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበራት፣ ሚዲያ፣ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች ችግሮችን ከሚያባብሱ ድርጊቶች ተቆጥበው ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለሀገር ሰላምና መረጋጋት የበኩላቸውን በጎ አስተዋጾ እንድታደርጉ፣
- ይህ ጉዳይ እየተባባሰ ሄዶ የከፋ ጥፋትና ችግር ከማስከተሉ በፊት የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ለንግግርና ውይይት እድል እንዲሰጡ ኢሰመጉ በእዚሁ አጋጣሚ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ